የአክሲዮን ማህበር መስራቾች ሀላፊነት

አሁን አሁን የአክሲዮን ማህበራት ምስረታ እየተበራከተ መምጣቱን ሁላችንም የምንታዘበው እውነታ ነው ። በአይነት እና በአላማ የተለያዩ አክሲዮን ማህበራት አሁንም በምስረታ ላይ ይገኛሉ ። ለምሳሌ ፡ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጡ የባንክ አክሲዮን ማህበራት ፡ የቢራ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበራት ፡ የትራንስፖርት አክሲዮን ማህበራት ፡ እና የ ኮንስትራክሽን ስራዎችን የሚሰሩ አክሲዮን ማህበራት ብለን ልንጠቅስ እንችላለን ። እነኚህ አክሲዮን ማህበራት የሚመሰረቱት ደግሞ መስራቾች በሚባሉ ሰዎች ነው ። ማህበሩን ከጥንስሱ ጀምሮ እስከ ምስረታው ድረስ ያለውን ሂደት የሚመሩት እነዚሁ መስራቾች ሲሆኑ ፡ ማህበሩ የሚሰማራበትን የስራ መስክ ትርፋማነት አስቀድመው የሚያጠኑት ፡ ፕሮስፐክተስ[1] የሚበትኑት ማስታወቂያ የሚያስነግሩት ፡ ብሎም በምስረታ ላይ በሚል ስም እና በራሳቸው ስም በባንክ አካውንት አስከፍተው ፡የአክሲዮን ገዢዎችን ገንዘብ የሚሰበስቡት እኚሁ መስራቾች ናቸው ። በመሆኑም አክሲዮን የምንገዛ ሰዎች የመስራቾችን ማንነት ፡ በሚገባ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ፡ በእጅጉ ማጥናት ያስፈልጋል ፡ ምክንያቱም አክሲዮን የምንገዛው መስራቾች ያወሩትን እና ያስነገሩትን አምነን ስለሆነ ነው ገንዘባችንን አውጥተን ፡ የማይታይና የማይጨበጥ አክሲዮን የምንገዛው ።

ነገር ግን የአክሲዮን ማህበሩ ምስረታ እንደታሰበው ስኬታማ ሳይሆን ፡ በንግድ ምዝገባ ሳይመዘገብ እና ስራ ሳይጀምር ፡ በምስረታ ላይ እያለ በተለያዩ ምክንያቶች ፡ አክሲዮን ማህበሩ ላይቋቋም ይችላል ። ስለሆነም የዚህ ፅሁፍ አላማ ፡ የአክሲዮን ማህበር የድርሻ ባለቤት እና የወደፊት ትርፍ ተካፋይ ለመሆን አስበው አክሲዮን የገዙ ሰዎች ፡ድንገት አክሲዮን ማህበሩ ሳይቋቋም ቢቀር ፡ የእኚህ ሰዎች እጣ ፈንታ ነው የሚሆነው? የሚለውን ጥያቄ ከ ንግድ ህጉ ድንጋጌዎች አንፀር መሰረታዊ ማብራሪያ መስጠት ነው ።

መስራቾች የገቡት ግዴታዎች

በንግድ ሕጉ ቁ. 308(1) መሰረት መስራቾች ማህበሩን ለማቋቋም ሲሉ ለገቡባቸው ግዴታዎች ፡ ለሶስተኛ ወገኖች ባንድነትና ሳይከፋፈል ያለወሰን ሀላፊዎች ናቸው ። ሶስተኛ ወገኖች ማለት ፡ ለምሳሌ ለስራ ማስኬጃ የሚሆን የገንዘብ ብድር ለእነኚህ መስራቾች ያበደሩ ሰዎች ወይም ፡ የተለያዩ የውል ግዴታዎች ከ መስራቾች ጋር የፈጠሩ ሰዎች (የቢሮ አከራይ፡ የመኪና አከራይ ወዘተ....) ስለሆነም ማህበሩን ለማቋቋም ሲሉ ለገቡባቸው ግዴታዎች መስራቾቹ ለሶስተኛ ወገኖች ባንድነትና ሳይከፋፈል ያለወሰን ሀላፊዎች ናቸው ሲል እነኚህ መስራቾች በግልም ሆነ በአንድነት ፡ በፍትህብሄራዊ ግዴታ/ገንዘብ እዳ/ እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ ማለት ነው ። ይህም ሀላፊነት ማህበሩ በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት ስለ ማህበሩ ሆነው በሰሩት ሰዎች ላይ የፀና ነው የሚሆነው ። በተጨማሪም ፡ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ማህበሩ ሳይቋቋም የቀረ እንደሆነ መስራቾች ለገቡት ግዴታዎችና ላደረጉት ወጪ አክሲዮን ለመግዛት የፈረሙትን ሰዎች የመጠየቅ መብት አይኖራቸውም ። ስለሆነም የአክሲዮን ማህበሩ ምስረታ ሂደት አልተሳካም እና የእዳ ተካፋይ ሁኑኝ ብሎ ማናቸውም መስራች የማህበሩን አክሲዮን ለመግዛት የተስማሙትን ሰዎች መጠየቅ አይችልም ማለት ነው ። ይህ ነጥብ ፡ ሕጉ በመስራቾች ላይ የሚጥለውን ከበድ ሀላፊነት ያመለክታል ።

በተጨማሪም ፡ በንግድ ሕግ ቁ. 309 (1) መሰረት መስራቾች ፡ ስለ ማህበሩ አቋቋም ለሕዝብ ያቀረቡት ማስታወቂያ እርግጠኛ ስለመሆኑ እና ለሚደርሱት ጉዳቶች ለማህበሩና ለሶስተኛ ወገኖች ባንድነት ሳይከፋፈል ጎላፊዎች ናቸው።። ነገር ግን በ ቁ. 309(2) መሰረት በመስራቾች ላይ ላይ የሚቀርብ ክስ ተጎጂው ጉዳቱን ወይም ሐላፊውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ 5 አመት ክስ ያላቀረበ እንደሆ በይርጋ ይታገዳል ። በሌላው በማንኛውም ሁኔታ ግን ጉዳት ከደረሰበት ቀን አንስቶ እስከ 10 ዐመት ክስ ካላቀረበ በይርጋ ይታገዳል ።

አክሲዮን ማህበሩ ሳይመሰረት ቢቀር

በ ንግድ ሕግ ቁ. 312 (1) መሰረት አክሲዮን ማህበር በሕግ እንደተቋቋመ የሚቆጠረው መጀመሪያ የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ ሲፈረም ነው።። ይህም ማለት ለአክሲዮን ማህበሩ የተመደበው መነሻ ካፒታል በሙሉ እንደሚከፈል ሰዎች በፊርማቸው አረጋግጠዋል ማለት ነው በእንግሊዘኛው fully subscribed ነው የሚባለው ። በመቀጠል በገንዘብ ከሚሸጡት አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ አንድ ሩብ ¼ በማህበሩ ስም እና አካውንት በአንድ ባንክ ሲገባ ነው ። እነዚህ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ አክሲዮን ማህበር አይመሰረትም ። በመሆኑም ፡ **በቁ.** 312 (3) መሰረት ፡- "ገንዘቡ በባንክ ከተቀመጠበት ቀን ጀምሮ እስከ (1) አንድ አመት ድረስ የንግድ ምዝገባው ያልተፈፀመ እንደ ሆነ ገንዘቡ አክሲዮን እንገዛለን ብለው ለፈረሙት ሰዎች ይመለሳል" ። ይህ ጊዜ የተላለፈ እንደ ሆነ እነዚህ የሚመለሱት ገንዘቦች ህጋዊ ወለድ ያፈራሉ ። ህጋዊ ወለድ በ ፍትህ ብሄር ህ/ቁ. 1751 መሰረት 9% ነው።። የሚመለሰውም በመስራቾች ጥንቃቄ ሆኖ እነሱም ባንድነት ሳይከፋፈል ፡ ሀላፊዎች ናቸው።።

[1] ፕሮስፐክተስ ማለት ፡ ሕዝብ አክሲዮን እንዲገዛ የሚደረገው ጥሪ መስራቾች ሁሉ የሚፈርሙበት የማህበር መግለጫ ነው ፡ ንግድ ህግ ቁ. 318

ስለሆነም ፡ በአጭር ጊዜ ትርፋማ እናደርጋችኋለን ብለው መስራቾች፡ በየሚዲያው አስተዋውቀው ፡ አክሲዮን ሸጥው ፡በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ሰብስበው ፡ ነገር ግን አክሲዮን ማህበሩን በንግድ ምዝገባ ሳያስመዘግቡ እና ወደስራ ሳይገቡ ፡ ገንዘቡን በባንክ አስቀምጠው አንድ አመት ካለፋቸው ፡ አክሲዮን ገዢዎች ገንዘባቸው ከ እነ ህጋዊ ወለዱ እንዲመለስላቸው መስራቾችን መጠየቅ ይችላሉ ማለት ነው ፡፡ በመሆኑም ፡ አክሲዮን ገዢዎች የላይኛው ሁኔታ መሟላቱን ተመልከተው፡ ገንዘባቸውን በጠየቁ ጊዜ ፡ መስራቾች ገንዘቡን ከእነወለዱ የመስጠት ሀላፊነት ተጥሎባቸዋል ፡፡

ሳሙኤል ግርማ

የሕግ አማካሪ እና ጠበቃ

በ ስልክ +251 911 190 299

በ ፌስቡክ https://fb.me/attorneysam

በ ቴላግራም https://t.me/lawyersamuel

ሳሙኤል ግርማ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Samuel Girma
Legal consultant and Attorney
+251911190299